# የህብረ ባህላዊ መርሆች

## Multicultural PrinciplesMulticultural Principles

**መርህ 1**
ሁሉም ግለሰብ በባህል ውስጥ የተመሰረተ ነው።

**መርህ 2**
በማህበረሰቦቹና በፕሮግራማችን ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች የተወከሉት ባህላዊ ቡድኖች ባህል ነክ ለሚሆኑ ፕሮግራሞች ተቀዳሚዎቹ ምንጮች ናቸው።

**መርህ 3**
ባህል ነክና የተስበጣጠረ ፕሮግራም፣ ስለተለያዩ የባህል ቡድኖች ትክክለኛ መረጃን ማወቅንና አልባሌ አስተያየቶችን ማስወገድን ይጠይቃል።

**መርህ 4**
የሥርዓተ ትምህርት ምርጫዎችን ለማድረግና ለማጽደቅ ለባህላዊ ተገቢነት ጉዳይ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው፣ ለእድገትም-ተገቢ የሆነ ተግባር ነው።

**መርህ 5**
እያንዳንዱ ግለሰብ በስብጥርጥር ሕብረተሰባችን ውስጥ ለማገልገል የሚያስፈልጉ ሞያዎችን በሚቀስምበት ወቅት፣ ግላዊ ማንነቱን ጠብቆ የመቆየት መብት አለው።

**መርህ 6**
እንግሊዝኛ ሳይሆን ሌሎች ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ልጆች የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ስኬታማነት እንዲኖራቸው፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርታቸው እንዲሟላ በሚደረግበት ወቅት የመጀመሪያ ቋንቋቸውም እንደዚያው መዳበሩ እንዲቀጥል ይጠይቃሉ።

**መርህ 7**
በባህላዊ ተገቢ የሆነ ፕሮግራም፣ ማህበረሰቡንና ተገልጋዮቹን ቤተሰቦች የሚመስሉና ኃላፊነትም የሚሰማቸው የሥራ ባልደረቦች እንዲኖሩ ይጠይቃል።

**መርህ 8**
ለልጆች የሚዘጋጅ በባህል ስብጥር የሆነ ፕሮግራም፣ ልጆች ለባህላዊ ልዩነቶች ግንዛቤን እንዲያዳብሩ፣ እንዲያከብሩ፣ እና አድናቆት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

**መርህ 9**
ባህል ነክ የሆነ፣ የተስበጣጠረ ፕሮግራም በተቋምና በግለሰብ ደረጃ የተመሰረቱ የቆዩ አግባብነት የሌላቸውን አስተያየቶች ይመረምራል እንዲሁም ይፈታተናል።

**መርህ 10**
ባህል ነክ የሆነ፣ የተስበጣጠረ ፕሮግራም እና ተግባሮች በሁሉም ሥርዓቶችና አገልግሎቶች ውስጥ የተካተቱ ሲሆኑ፣ ለሁሉም ጎልማሳ ሰዎች ህጻናት ጠቀሜታ አላቸው።

**Related documents**
*Diversity and Classroom Celebration Policy*
*Diversity and Classroom Celebration Procedure*

**Resources**
Head Start Multicultural Principles
[http://eclkc.ohs.acf.hhs.gov/hslc/hs/resources/ECLKC_Bookstore/PDFs/Revisiting%20Multicultural%20Principles%20for%20Head%20Start_English.pdf](http://eclkc.ohs.acf.hhs.gov/hslc/hs/resources/ECLKC_Bookstore/PDFs/Revisiting%20Multicultural%20Principles%20for%20Head%20Start_English.pdf)